# አይ ሽምብራ!



መለኮት ፈቅዶ ቢዘራህ ተጫፍ ጫፍ እንደ እንደ ጤፍ ስንዴ አዝመራ፣
ጓያ አሽመድምዶ ሊያደርቅህ ተሰርዶ መክሮ ወጥመድን ሲሰራ፣
ምነዋ ያለታሪክህ ያለተፈጥሮህ እንደ ነቀዘ ብሳና ፈዘዝካ?

ለዓመታት ሲጠረጥሩህ ጥርስ ሳትሰብር ስለተበላህ ዝምብለህ!
ግመሮች ዘምተውብሃል ነቃቅለው ተምድር ዘርህን ሊያጠፉህ!

አይ ሽምብራ!

ተጋለ ምጣድ በትነው ለብዙ ዓመታት በእሳት ነበልባል የቆሉህ፣
ጩኸትን ተላንቃህ  ሞጭልፈው በዓለም መድረክ ላይ ሲቀሙህ፣
ምነዋ የዲዳም ያህል የብሶት ድምጥን ማሰማት አቃጠህ?

አይ ሽምብራ!

በእሳት ነበልባል ተገርፈህ ተቃጥለህ አረህ ስጠፋ፣
ሽምብራ ፈጀኝ እያለ አፉን ቦርግዶ ይጮኻል መቆያ!

ዓለምም ተዓይኗ ጀሮዋን የምታምን ፍርድ-ገምድል ጉድ ናትና፣
ታዳምጣለች የሚቆላውን ለፍላፊ የተቆላውን ሽምብራ እረስታ!

አይ ሽምብራ!

የእንቅቡ ተዳር ቁጭ ብሎ ሳይነኩት እንደ ፈንድሻ ሲንጣጣ፣
ዘወትር በጋለ ምጣድ ሲቆሉህ ምነው ሆድ ይፍጀው ብልህ ዝም አልካ!

ዝም ያለን እንኳን የሰው ልጅ እጁን  በሀጥያት ያጠበው፣
ሁሉንም እኩል የሚያየው እግዜርም  በደል ብሶቱን ሳይሰማው፣
በዚች መሬት ላይ እንደሚያልፍ ምነው ሽምብራ አጣሃው?

አይ ሽምብራ!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ሰኔ ሁለት ሺ አስራ ሶስት ዓ.ም.